MoWE/JICA
The Project for Rural Water Supply, Sanitation and Livelihood Improvement through Dissemination of Rope Pumps (RPs) for Drinking Water (WAS-RoPSS)

ዕትመ ቁ 2 ሐምሌ 24/2005

# ዜና ዉሃን በጥረቴ

## - የተሻለ ኑሮ በገመድ ፓምፕ-

ገመድ ፓምፕን ለመጠጥ ዉሃ በማሰራጨት የገጠርን የንጹህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት፤ንፅሕና (ሳኒቴሽን) እና ኑሮን የማሻሻል ፕሮጀክት

**(WAS-RoPSS)**

(ዉሃን በጥረቴ)

## የክቡር ሚኒሰትር ዴኤታ አስተያየት

የገመድ ፓምፕ ለኢትዩጲያ ዉሃ አቅርቦት በተለይም የከርሰምድር ዉሃ ሀብት በቅርብ ጥልቀት ባለበት አከባቢ ትክክለኛ የሆነ ቴክኖሎጂ ነዉ ብለዉ የዉሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ ከበደ ገርባ ገለፁ፡፡ ከእኛ ዜና ዉሃን በጥረቴ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ አያይዘዉ ሲናገሩ የገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ ተበታትኖ ለሚኖር ህብረተሰብ ፤የመንገድ መሰረተ ልማት ያልተስፋፋበት አከባቢና በሌሎች የዉሃ አቅርቦት ዘዴዎች ማዳረስ ያልተቻለዉን ህብረተሰብ በቀላል ወጪ የዉሃ አቀርቦትን ለማስተናገድ ጥሩ አማራጭ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ ከፍተኛ የሆነ የፋይናንስና የአፈፃፀም ችሎታ የማይጠይቅ በመሆኑ የእደገትና ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራምን ለማሳካት እንዲሁም የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ዕቅድ አጋዥ እና ከፍተኛ አስተዋጾኦ የሚያደረግ ነዉ፡፡አስተዋፅኦዉ ለመጠጥ ዉሃ፤ሳኒቴሽንና ሥነ-ንፅህና ብቻም ሳይሆን ለምግብ ዋስትና ጥረታችንም ጭምር ነዉ፡፡ሚኒስትሩ ይህ የገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ ማሳደግ እና መስፈርቱን ባሟላ ሁኔታ




መጠቀም አስፈላጊ ነዉ ብለዋል፡፡ይሁንና ይህ የመጨረሻ ግብ መሆን እንደሌለበት ጨምረዉ አስገንዝበዋል፡፡የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዳችን ሁለት አመት የቀረው ከመሆኑ አንፃር ይህንን ቴክኖሎጂ ለህብረተሰቡ በፍጥነት በማስተዋወቅ እንዲጠቀም ማድረግ እንዳለብን አበክረዉ ገልፀዋል፡፡

## 4 ለፕሮጀክቱ ግብ የተመረጡ ወረዳዎች!

ከባለድረሻ አካላት ጋር በመመካከርና በተደረገዉ የከርሰምድር ዉሃ እምቅ ሃብት እንዲሁም የወረዳዎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅም ጥናት መሰረት አራት ወረዳዎች ከሲዳማ ዞን ዳሌ፣ከጌድዮ ዞን ይርጋጨፌ፣ ከጉራጌ ዞን መስቀን እና ከወላይታ ዞን ዳሞት ፑላሳ ተመርጠዋል፡፡




## ገመድ ፓምፕ እና ፕሮጀክቱን ስለማስተዋወቅ

የሚከተሉት ምልክትና መልዕክት ገመድ ፓምፕን እና ፕሮጀክቱን ለማስተዋወቅ ብሎም ለማሰራጨት የምንጠቀምባቸዉ ናቸዉ፡፡

የፕሮጀክቱ ምልክት

### አጭር መልዕክት

**የተሻለ ኑሮ በገመድ ፓምፕ**

### የፕሮጀክቱ ቅፅል ስም

**ዉሃን በጥረቴ**

## ገመድ  ፓምፑን በተመለከተ በሶስት ክልሎች ላይ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት (ከሚያዚያ 21 እስከ ሐምሌ 20/2005)



የፕሮጀክት ቡድን በአሁኑ ጊዜ ያለዉን የገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ፣ የገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች የሚፈልጉትን ማሻሻያዎች እና የሚመረቱትን ሞዴሎች በዝርዝር ለማየት በሶስት ክልሎች ያሉትን የገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎችና አምራቾች ላይ የአሰሳ ጥናት አካሄዷል፡፡ በዚሁ መሰረት ቡዱኑ የተለያዩ የቴክኒክ እና የዲዛይን ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉ ግንዛቤ ወስዷል፡፡ለምሳሌ ፓምፑ በጀርካን ዉሃ መቅዳት እንዲመች ማድረግ ፣ፓምፑ ትክክለኛ የሆነ ርዝመት እንዲኖረዉ፣ዉሃ ወደ ጉድጓድ ተመልሶ እነዳይገባ ማድረግ፣የፓምፑ መለዋወጫዎች (ገመድ፣ኩሽኔት፣ፒስተን እና ብሎን)ቧንቧዎች እና የመሳሰሉት ረጅም ጊዜ የሚያገለግሉ እና በቀላሉ የሚገኙ መሆን አለባቸዉ፡፡አንዳንድ የአመራረት ችግሮች ለምሳሌ ጥሩ ያልሆነ ብየዳና ትክክለኛ ያልሆኑ ዕቃዎችን ወይም መለዋወጫጫዎች የመጠቀም ችግሮች ይታያሉ፡፡በተጨማሪም ቡዱኑ ከጉድጓድና ጉድጓድ መከደኛ ጋር በተያያዙ ሁኔታዎች በገመድ ፓምፖች ላይ ብዙ ችግሮች መኖራቸዉን ተገንዝበዋል፡፡ይህም ትክክለኛ ያልሆነ የዉሃ ጉድጓድ ዲዛይን፣ ከቦታ አመራረጥ ችግር የተነሳ የጉድጓድ መፍረስ፣ የዉሃ ወደ ጉድጓድ ተመልሶ ምግባት ፣በበጋ ጊዜ የዉሃ መዉረድ(ዝቅ ማለት)ወዘተ የተስተዋሉ ችግሮች ናቸዉ፡፡እንድሁም የገመድ ፓምፑ ብልሽት ከአገጣጠም ችግር ጋር የተያያዘ የብልሽት ሁኔታም ያጋጥማል፡፡ለምሳሌ ገመዱ በጣም ላላ ተደርጎ ወይም ደግሞ ከርሮ መታሰር የለበትም፡፡የወረዳ ጽ/ቤቶች እና ተጠቃሚዎች የገመድ ፓምፕ በቀላሉ የሚሰራ መሆኑ ጥሩ ነዉ ቢሉም የተደረገዉ ጥናት እንደሚያመለክተዉ በገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች የጥገና አቅም ማነስ ምክንያት በአግባቡ ጥቅም ላይ እየዋለ አለመሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡ለዚህም የተጠቃሚዎች የስልጠና ማጣት፣የመሳርያዎች እና የመለዋወጫዎች እጥረትና በአከባቢ ባለዉ ገበያ የማይገኙ መሆናቸዉ ምክንያት ተደርጎ በዋናነት ይወሰዳል ፡፡ከመጠጥ ዉሃ ጥራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችም ይነሳሉ፡፡አብዛኞቹ ተጠቃሚዎች እኛ ለዉሃ ጥራት በቂ ትኩረት እንሰጣለን ይላሉ፡፡ጥቂቶቹ ደግሞ የገመድ ፓምፕ ዉሃን ለመጠጥ አንጠቀምበትም ብለዋል፡፡ ምክንያቱም ለመስኖ ዉሃ የሚዉል ብቻ ነዉ ብለዉ በማስባቸዉ ፡፡ነገር ግን የፕሮጀክት ቡድኑ የገመድ ፓምፕ ዉሃ ጥራትን በሚመረምርበት ጊዜ ጉድጓድ ዉስጥ ያለዉ ዉሃ በቤት ዉስጥ በጀሪካን ከተቀመጠዉ ጋር ሲነፃፀር በጀሪካን ዉስጥ የተቀመጠ ዉሃ ንፅህናዉ የጉድጓዱ ተሽሎ ተገኝቷል፡፡ባአብዛኛዉ አፍረዴቨ ፓምፕ ከገመድ ፓምፕ ለመጠጥ ዉሃ የተሻለ ነዉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይሁንና የፕሮጀክት ቡድኑ ይህ አስተሳሰብ ሁልጊዜ ትክክል አለመሆኑን ተረድቷል፡፡ከዚህም በመነሳት የፕሮጀክት ቡድኑ ዉሃን ከምንቀዳበት እስከ ምንጠቀምበት ድረስ ያለዉ የዉሃ ብክለት ምንጭ ላይ ጥናት መደረግ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ በአጠቃላይ ወደ ፊት የገመድ ፓምፑን ለማሰራጨት እንዴት መኬድ እንዳለበት የፕሮጀክት ቡድኑ ከዚህ አሰሳ ጥናት ብዙ ትምህርት አግኝቷል፡፡





### በሰኔ እና በሐምሌ የተደረጉ ሥራዎች

| | |
|---|---|
| በሰኔ | – የዉሃ ጉድጓድ ቁፋሮ (ለማሻሻያ ሥራ) |
| በሰኔ | – ፕሮጀክቱ የሚሰራበት ወረዳዎች መረጣ |
| በሐምሌ | – 2ኛዉ የጋራ አስተባባሪ ኮሚቴ ስብሰባ |
| በሐምሌ | – 2ኛዉ የመሪ ኮሚቴ ስብሰባ |
| በሐምሌ | – የገመድ ፓምፕ ማሻሻያ እና የገመድ ፓምፕ ሞዴሎች ማሰባሰብ፤የፕላስቲክ ፋብሪካ ጉብኝት እንዲሁም የገመድ ፓምፕ አምራቾች ስብሰባ |

### በነሐሴ እና በሐምሌ የሚደረጉ ሥራዎች

- የገመድ ፓምፕ መሻሻያ፤ፕላስቲክ ፋብሪካን መጎብኘትና፤ከአምራቾች ጋር ስብሰባ ማድረግ
- የፕሮጀክት ሂደት ሪፖሪት ቁ 1
- የፕሮጀክት ማስተዋወቂያ በራሪ ወረቀት
- የፕሮጀክት ዌብሳይት መመስረት
- መሰረታዊ የሆነ የቤዝላይን ጥናት ዝግጅት



ቃለ ምልልስ ዉሃ ቀድተው ከሚመለሱ እንስቶች ጋር



ቃለ ምልልስ ከገመድ ፓምፕ አምራቾች ጋር

ማንኛዉንም አስተያየት፣ጥያቄዎች፣ሐሳብ ካላችሁ በዚህ አድራሻ ተጠቀሙ

ጃይካ ሮፕ ፓምፕ ፕሮጀክት
ክፍል # 016, ዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር
ስልክ: +251 - (0)11-651-1455
ሞባይል: +251 - (0)935-353210/11

Webiste
【MoWE】http://www.mowr.gov.et/
【JICA】http://www.jica.go.jp/ethiopia/english/office/index.html
【EWTEC】http://www.ewtec.org.et/
E-mail : jica.ropepump.ethiopia@gmail.com